የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 22
ADDIS ABABA 7th February, 2005

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፯/፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግሥትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ..ገጽ ፫ሺ፴፱

CONTENTS

Proclamation No. 437/2005

A Proclamation to ratify the Treaty signed on Touris Cooperation with The Republic of the Sudan….. Page 3039

### አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፯/፲፱፻፺፯

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አ ዋ ጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የቱሪዝም ስምምነት ግንቦት ፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. በካርቱም ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ አገሮች ህጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ በመገለጹ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### PROCLAMATION NO. 437/2005.

### A Proclamation for the ratification of the agreement between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Republic of Sudan on Tourism Cooperation

**WHEREAS,** the Treaty on Tourism Cooperation between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and The Republic of the Sudan is signed in Khartoum 11th May 2002 ;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Treaty that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Represent - atives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has rarified the said Treaty at its session held on 6th day of January, 2005

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፯/፲፱፻፺፯» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ በካርቱም ከተማ ግንቦት ፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፴ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Tourism Cooperation Treaty between The Federal Democratic Republic of the Ethiopia and the Republic of Sudan Ratification Proclamation No.437/2005."

## 2. Ratification of the Treaty

The Treaty on Tourism Cooperation Signed in Khartoum on 11th May 2002, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of the Sudan is ratified.

## 3. Responsibility of the Ethiopian Tourism Commission

The Ethiopian Tourism Commission is hereby empowered to implement this Treaty.

## 4. Effective Date

The Proclamation shall enter into force as of 7th day of February, 2005.

**Done at Addis Ababa, the 7th day of February, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**